# ስልጠና፡- ክህሎት 2. ውጤታማ የጊዜ አጠቃቀም

©አጥቢያ ዶት ኮም

“ለሁሉ ዘመን አለው። ከሰማይ በታችም ለሆነ ነገር ሁሉ ጊዜ አለው።” መጽሐፈ መክብብ 3፥ 1

1. መግቢያ
    - የተለመዱ አባባሎች
        - ጊዜ የለኝም /አጥሮኛል/
        - እገሌ(ሊት) እንዴት ጊዜ ቢሞላላቸው ነው
        - የአበሻ ቀጠሮ
        - እሱ ያለው ነው የሚሆነው፣ ምን አስጨነቀኝ
    - መሰረታዊ ምክንያቶች
        - ግድ የለሽነት / ድንዛዜ
        - የጊዜን ጠባያት በጥልቀት አለመረዳት
        - ውጤታማ የአጠቃቀም ልምድ አለመኖር
2. የጊዜ ጠባያት
    1. የእግዚአብሔር ስጦታ ነው
        - በቸርነትህ ዓመትን ታቀዳጃለህ... መዝ 65፥11
        - “ጌታ ቢፈቅድ ብንኖርም ይህን ወይም ያን እናደርጋለን ማለት ይገባችኋል” ያዕ 4፥15
    2. ገለልተኛ ነው
        - ለአንዱ የሚሰጠው ከሌላው አይረዝምም፣ አያጥርም
        - አንዱ ቀን ከሌላው ተለይቶ ቅዱስ ወይም እርኩስ አይደለም (የምናደርጋቸው ነገሮች ግን ቀኑን በጥሩነት ወይም በመጥፎነት እንዲታወሱ ያደርጋሉ)
    3. ውሱን ነው
        - ይህንን ካደረጉ ያንን ማድረግ አይቻልም
    4. የማይቀመጥ ነው
        - ~~ጊዜ ወርቅ ነው~~
        - ጊዜ ከባከነ ተመልሶ መገኘት አይችልም
3. ውጤታማ የጊዜ አጠቃቀም
    1. መፈተሽ (ውይይት፡-ጊዜያችንን የምንጠቀመው ለምን ጉዳይ ነው?)
        - መደበኛ /መሰረታዊ
            - ስራ/ትምህርት
            - መሰረታዊ ሰብአዊ ፍላጎቶች (መብልና መጠጥ፣ እንቅልፍ፣ እራስን እና ቤተሰብን መንከባከብ)
            - ለጸሎት

- ኢ- መደበኛ /በተለምዶ "ትርፍ ጊዜ" የሚባለው/
    - ለእረፍት (የአካል እና አእምሮ መታደስ)
    - ለመዝናናት
    - ለእውቀት ማግኛ
    - ለማኅበራዊ ጉዳዮች
    - ለመንፈሳዊ አገልግሎት
    - ሶሽያል ሚድያ

2. የጊዜ አጠቃቀም ብቃትን ማጎልበት
    - ለማንኛውም ነገር 3 የጊዜ ክፍሎች ያስፈልጉታል
        - ሲታሰብ / ሲታቀድ
        - ሲተገበር
        - ሲፈተሽ
    - ጉዳዮች ከአስፈላጊነት እና አስቸኳይነት አንጻር መመዘን
        - አስፈላጊ + አስቸኳይ - በተቻለ ፍጥነት መተግበር
        - አስፈላጊ + አስቸኳይ ያልሆነ - መቼ እንደሚሰራ ወስኖ ጊዜ የጊዜ ሰሌዳ ላይ ማስቀመጥ
        - አስፈላጊ ያልሆነ + አስቸኳይ - በተሻለ ለሚመለከተው ማስተላለፍ /delegation/
        - አስፈላጊ ያልሆነ + አስቸኳይ ያልሆነ - መተው
    - ልዩ ልዩ
        - አእምሯችን በተፈጥሮ ንቁ የሚሆንበትን ጊዜ መለየት
        - ለነገ ማለትን መተው
        - ኃላፊነትን ማካፈል
        - እምቢ ማለትን መልመድ
            - የማይጠቅም መረጃንና ተሳትፎዎች
            - ከዋናው እቅዳችን ውጪ ከሆነ

3. የጊዜ ድልድልን መለማመድ /በሳምንት - “ጌታ ቢፈቅድ ብንኖርም ይህን ወይም ያን እናደርጋለን ማለት ይገባችኋል” ያዕ 4፤ 15
    1. ያለፈውን ሳምንት ለመፈተሽ
        - ጠንካራ (እንዴት እናጎልበተው?)
        - ደካማ (ምን ተማርንበት?)
    2. አጠቃላይ ርዕያችንን እና የረዥም ጊዜ ጉዳዮችን መቃኘት
    3. የቀጣዩን ሳምንት ስራዎች መቃኘት
        - ስራዎች የሚፈልጉትን ጊዜ መገመት
        - በካሌንደር ላይ ጊዜ መመደብ
        - ማሳሰቢያ፡- መጠባበቂያ /ያልተደለደለ ጊዜ ሊኖረን ይገባል
    4. ፈጣሪያችንን ማሰብ
        - ስላለፈው ማመስገን
        - ስለመጪው ጥብብን ማስተዋልን እና እገዛን መለመን

4. ተቋማዊ እይታ
    1. ተቋማዊ የጊዜ ብክነት የሚታይባቸው
        1. ስብሰባ
        2. የጉዳይ አስተዳደር
        3. እቅድ እና ትግበራ
        4. ክትትል እና ግምገማ (ቁጥጥር)
        5. . . .
    2. መፍትሔው
        1. ውጤት ተኮር ተቋማዊ ባህልን መፍጠር
        2. ብክነትን ያስወገደ ተቋማዊ ባህልን መፍጠር
        3. ስልት እና ትግበራን ማጣጣም
        4. ማንቃት፣ ማብቃት፣ ሥርዓት መዘርጋት